**የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ**
**ETHIOPIAN HUMAN RIGHTS COUNCIL**

ኢሰመጉ የቆመው ለዲሞክራሲ፣ ለሕግ ልዕልናና ለሰብአዊ መብቶች መከበር ነው::
**EHRCO stands for democracy, the rule of law and the respect of human rights.**

ጥር 1 ቀን 2000 ዓ.ም

# ሕጋዊ መፍትሔ የሚሻ ሕገወጥ ድርጊት - አርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ

## 105ኛ ልዩ መግለጫ

## መግቢያ

የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 16 «ማንኛውም ሰው በአካሉ ላይ ጉዳት እንዳይደርስበት የመጠበቅ መብት አለው» ሲል ይደነግጋል:: የሰዎች የአካል ደህንነት የመጠበቅ መብት የማይደፈርና የማይገሰስ መሆኑን የህገመንግስቱ አንቀጽ 14 ያረጋግጣል:: የህገመንግስቱ አንቀጽ 31 ደግሞ ማንኛውም ሰው ለማንኛውም አላማ በማህበር የመደራጀት መብት እንዳለው ይደነግጋል:: እንደዚሁም ህገመንግስቱ በአንቀጽ 41 (1) ላይ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በሀገሪቱ ውስጥ በማንኛውም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በመሰማራት ለኑሮው የሚያስፈልገውን ገቢ የማግኘትና የመጠቀም ህገ መንግስታዊ መብት እንዳለው ያረጋግጣል::

በሌላ በኩል ደግሞ ማንኛውም ሰው በህግ እውቅና ያገኙት መብቶቹ በህግ ከተደነገገው ውጪ እንዳይጣሱበት መጠበቅ መሰረታዊ የህግ የበላይነት መርህ የሚጠይቀው ግዴታ ነው:: እነዚህን ህገመንግስታዊ ድንጋጌዎች የማክበርና የማስከበር ግዴታ የሁሉም ወገኖች ቢሆንም የመንግስት ድርሻ ግን ከሁሉም የላቀ መሆኑ አያጠያይቅም::

ይሁን እንጂ እነዚህን ህገ-መንግስታዊ ድንጋጌዎች በሚቃረን መልኩ በርካታ ግለሰቦች በህግ ከተደነገገዉ ሥርዓት ውጭ አካላዊ ድብደባ ተፈጽሞባቸው፣ ንብረቶቻቸው ወድመውባቸውና የተለያዩ በደሎች ተፈጽመውባቸው ለመንግሰት አካላት ቢያመለክቱም መፍትሄ ሊያገኙ አልቻሉም::

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ(ኢሰመጉ) በዚህ 105ኛ ልዩ መግለጫው በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት አርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ በላንቴ ቀ/ገ/ማህበር ውስጥ በሚገኙ አንዳንድ የወላይታ ብሄረሰብ አባላት በሆኑ አርሶ አደሮች ላይ በአካባቢው ኃላፊዎች በመታገዝ የኦቾሎ ብሄረሰብ አባላት ያደረሱባቸውን የሰብአዊ መብቶች ጥሰት አጣርቶ እንደሚከተለው አቅርቧል::

## ዝርዝር

በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች ህዝቦች ክልላዊ መንግስት በጋሞ ጎፋ ዞን በአርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ በላንቴ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ውስጥ በወላይታ እና በኦቾሎ ብሄረሰብ አባላት መካከል በ1992 ዓ.ም በይዞታ ይገባኛል ሰበብ በተፈጠረ ግጭት በወላይታ ብሄረሰብ ተወላጆች ላይ የህይወት መጥፋት፣ የንብረት መውደም እና የወላይታ ብሔረሰብ

ተወላጆችን ከእድር እንደማስወጣት ያሉ የተለያዩ የማህበራዊ ህይወት ችግሮች ደርሰው ነበር::

ይህንን ተከትሎ ከእድር እንዲወጡ የተደረጉት የወላይታ ብሄረሰብ ተወላጆች ከሌሎች ብሄረሰብ አባላት ጋር በመሆን አዲስ እድር በማቋቋም እየተረዳዱ የቆዩ ሲሆን ታህሳስ 3 ቀን 1999 ዓ.ም በላንቴ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ውስጥ ከኦቾሎ ብሄረሰብ እድር ውጭ ሌላ እድር ሊኖር ስለማይገባው በአስቸኳይ እንድታፈርሱ የሚል ትእዛዝ ከላንቴ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ሊቀመንበር ከአቶ አለማየሁ አሻ እና ከኦቾሎ ባህል አስፈጻሚዎች ለእድሩ አመራር ኮሚቴዎች ትእዛዝ መተላለፉን እና ለማፍረስም ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ምክንያት በተለያዩ ጊዜያት የእድሩን መገልገያ እቃዎች ለመውሰድ ሙከራዎች መደረጋቸውን እና ይህንንም ህገወጥ ድርጊት በወቅቱ ከወረዳ እስከ ዞን አስተዳደር ድረስ ቢያሳውቁም መፍትሄ ሊያገኙ አልቻሉም::

ለችግሩ መፍትሄ ከማምጣት ይልቅ የአካባቢው አስተዳደር ተወካዮች የሆኑት የቀበሌው የአመራር አካላት በድርጊታቸው ቀጥለውበታል:: የአካባቢው አስተዳደር ተወካዮች ከድርጊታቸው ከመቆጠብ ይልቅ የአቅም ግንባታ ሚኒስቴር *«በገጠር ወረዳ እና ቀበሌ የመልካም አስተዳደር ጥያቄ»* በሚል በ1998 ዓ.ም ባወጣው ማኑዋል ገጽ 49 ላይ በዲሞክራሲያዊ፣ በጋራ መግባባትና በተሳትፎ አሰራር ዙሪያ መደረግ የሌለባቸው ነገሮች በሚል ንኡስ ርእስ ስር «...ህዝቡ (ጥፋተኛ ያለውን ሰው) በራሱ መንገድ የፈለገውን ማህበራዊ ቅጣት ሊወስንና ያለአስተዳደሩ ጣልቃ ገብነት ሊፈጽመው ይችላል» በማለት የሚገልጸውን በመንተራስ ብሄረሰቡ በባህሉ መሰረት ለባህሉ አልገዛም ያለውን በፈለገው መንገድ መቅጣት ይችላል በማለት በአካባቢው የሚኖሩትን የወላይታ ብሄረሰብ አባላት ሰርተው እንዳይኖሩ ሲሞቱ እንኳን እንዳይቀበሩ ከፍተኛ ግፍ እየፈጸሙባቸው ይገኛሉ::

በዚህም መሰረት የአካባቢውን ነዋሪ በተለያየ ጊዜ ስብሰባ በመጥራት «...ከዚህ በፊት ማዕቀብ የጣልንባቸው ሰዎችና ለእነሱ ምስክር በመሆን የረዷቸውን ሰዎችን በቤታቸው የሚገኘውን ንብረታቸውን እናውድም፤ አትክልታቸውንም እንጨፍጭፍ፡ እነሱን አሳደን ማስረጃ ማሳጣት አለብን፤ በዚህ በባህላችን ማዕቀብ ያልተሳተፈ ሰው ላይ ማዕቀብ እንጥልበታለን...» በማለት ህዝቡን አነሳስተው በርካታ የወላይታ ብሄረሰብ አባላት ንብረት የሆነ የሙዝ ተክል በተለያየ ጊዜ አውድመዋል፣ ግለሰቦችም በመንግስትና በህዝብ መገልገያዎች እንዳይጠቀሙ ተደርገዋል፣ ከማህበራዊ ህይወታቸውም ተገለዋል፣ የሞቱ እንዳይቀበሩ ተደርገዋል፣ ከኦቾሎ እድር ሌላ ማቋቋም አይቻልም በሚል የወላይታ ብሄረሰብ አባላት ያቋቋሙት እድር በሀይል ፈርሶ የእድሩ መገልገያ ዕቃዎች ድንኳኑን ጨምሮ ተወስደውባቸዋል፣ ለአካላዊ ጥቃትና ለስደት ተዳርገዋል:: ይህንኑም ኢሰመጉ በስፍራው ተገኝቶ በማጣራት የጉዳዩን አሳሳቢነት በመግለጽ ድርጊቱ እንዲቆምና ዘላቂ መፍትሄ እንዲፈለግለት በመጠየቅ በተለያዩ መግለጫዎቹ ማሳወቁ የሚታወስ ነው::

ይሁን እንጂ ይህ የጥፋት ድርጊት አሁንም አልቆመም:: ህዳር 6 ቀን 2000 ዓ.ም የቀ/ገ/ማህበሩ አመራር ነዋሪው በድጋሚ በተጠራበት ስብሰባ የወላይታና የሸዋ በር መረዳጃ እድር አባል የሆኑትን ሰዎች በዱላ በመደብደብ ጉዳት አድርሰውባቸዋል:: ተጎጂዎቹ የተፈጸመባቸውን የሰብአዊ መብት ጥሰት ለወረዳና ለዞን በማመልከት ላይ እያሉ የቀ/ገ/ማህበሩ አመራሮች በየቤታቸው በመዞር «አልከስም፣ አልመሰክርም፣ እድሩንም አፈርሳለሁ፤ በአጠቃላይ ጥፋተኛ ነኝ በማለት ማመልከቻ አስገቡ አለዚያ

አትኖሩም» በማለት ሲያስፈራሯቸው ቆይተው ህዳር 30 ቀን 2000 ዓ.ም ከዚህ በታች ስም ዝርዝራቸው የተገለጸውን የወላይታ ብሄረሰብ አባላት እና የሸዋ በር መረዳጃ እድር አባላት 6 ሄክታር ማሳ ላይ የነበረውን አትክልት ጨፍጭፈውባቸዋል፡፡

**ድብደባና ማሳደድ**

| ተ.ቁ | የተደብዳቢው ስም | የደረሰበት ጉዳት |
|---|---|---|
| 1 | መና ጨቃሎ | በተፈጸመበት ድብደባ ግራ እጁና ልዩ ልዩ ሰውነቱ ላይ ጉዳት የደረሰበት |
| 2 | አድማሱ ኦንጫ | በዱላ ከተደበደበ በኋላ እያሳደዱ ጥይት ተኩሰውበት ያመለጠ |
| 3 | አሰፋ ካሳዬ | ከተራ ቁጥር 2 ጋር ተመሳሳይ ድርጊት የተፈጸመበት |
| 4 | ፍቅሩ መና | በድብደባ ጭንቅላቱ የተፈነከተ |
| 5 | ተሻለ ጮላፎ | በተለያዩ የሰውነት ክፍሎቹ ላይ ድብደባ የተደረገበት |

**የንብረት መውደም**

| ተ.ቁ | የተጎጂው ስም | ዕድሜ | የደረሰው ጉዳት መጠን | የደረሰው ጉዳት በገንዘብ ሲተመን |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ በረታ ባላ ጫኪሶ | 66 | በ1 ሄክታር ላይ ተተክሎ የነበረው ሙዝ አቮካዶ ማንጎ እና ሌሎች አትክልቶች ተጨፍጭፈዋል | 70 ሺህ ብር |
| 2 | አቶ ማንታ አይመሎ አነቦ | 60 | በሩብ ሄክታር ላይ ተተክሎ የነበረ ሙዝ ሙሉ በሙሉ ተጨፍጭፏል | 20 ሺህ ብር |
| 3 | አቶ ካፈቻ ዶሳ አንጄሮ | 60 | በሩብ ሄክታር ላይ ተተክሎ የነበረ ሙዝ ማንጎ አቮካዶ ተጨፍጭፏል | 60 ሺህ ብር |
| 4 | አቶ ዲታ ዲጋዶ ዲባ | 65 | በ1 ሄክታር ላይ ተተክሎ የነበረ ሙዝ ማንጎ አቮካዶ ሎሚ ተጨፍጭፏል | 50 ሺህ ብር |
| 5 | አቶ ኤልያስ ሊባቶ ገለሰ | 40 | በ1 ከግማሽ ሄክታር ላይ ተተክሎ የነበረ ሙዝ ማንጎ አቮካዶ ተጨፍጭፏል | 50 ሺህ ብር |
| | ጠቅላላ ድምር | | | 250,000 ሺህ ብር |

## ማጠቃለያ

- ከዚህ በላይ በዝርዝር እንደተመለከተው ግለሰቦቹ የሌላን ብሄረሰብ ባህል ካላከበራችሁ ተብለው በአካባቢው አስተዳደር ተወካዮች ቀስቃሽነት ሰርተው እንዳይኖሩ ሲሞቱ እንኳን እንዳይቀበሩ ከፍተኛና ተደጋጋሚ ግፍ እየተፈጸመባቸው የመንግስት ያለህ እያሉ ይገኛሉ፡፡ በወላይታ ብሄረሰብ ተወላጆች ላይ እየተፈጸመ ያለው ይህ ግፍ ደግሞ በአገሪቱ ህገመንግስት የተቀመጠውን የህግ የበላይነት የሚጻረር በመሆኑ ኢሰመጉ ያወግዘዋል፡፡ መንግስትም ህገመንግስቱን የማስከበርና የዜጎችን የህይወት፣ የአካል ደህንነትና

የንብረት መብቶችና ነጻነቶች በማስጠበቅ በኩል ያለበትን ህገመንግስታዊ ግዴታ በአግባቡ እንዲወጣ ኢሰመጉ በድጋሚ ይጠይቃል፡፡

- ከዚህም በተጨማሪ ከላይ በዝርዝር የተገለጹትን የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች የፈጸሙ፣ ዜጎችን ከህግ አግባብ ውጭ ከማህበራዊ ኑሯቸዉ እንዲገለሉ ያደረጉ፣ ድብድባ የፈጸሙና ንብረት ያወደሙ፣ እንደዚሁም ለዚህ ህገወጥ ተግባር ህዝብን ያነሳሱ የአካባቢ ባለስልጣናት በህግ እንዲጠየቁና ድርጊታቸውም እንዲቆም፣ በተደጋጋሚ አቤቱታ ቀርቦላቸው መፍትሄ ያልሰጡ የወረዳና የዞን ባለስልጣናትም በህግ እንዲጠየቁ፣

- በግፍ ለተደበደቡና ለቆሰሉ፣ እንዲሁም ንብረታቸውን ያላግባብ ለተወረሱና ለወደመባቸው ሁሉ ተገቢ ካሳ እንዲከፈላቸው፣

- የአቅም ግንባታ ሚኒስቴር *«በገጠር ወረዳ እና ቀበሌ የመልካም አስተዳደር ጥያቄ»* በሚል በ1998 ዓ.ም ባወጣው ማኑዋል ላይ «...ህዝቡ (ጥፋተኛ ያለውን ሰው) በራሱ መንገድ የፈለገውን ማህበራዊ ቅጣት ሊወስንና ያለአስተዳደሩ ጣልቃ ገብነት ሊፈጽመው ይችላል» በማለት የሚገልጸው አረፍተ ነገር እንደገና ታይቶ እርምት እንዲደረግበትና ይልቁንም ማንም ወገን የዜጎችን ሕገ መንግስታዊ መብት የሚጋፋ ማንኛውንም ተግባር መፈጸም እንድማይችል በግልጽ እንዲነገር፣ እንዲሁም

- በወረዳው የሚኖሩ የወላይታ ብሄረሰብ አባላትና የኦቾሎ ብሄረሰብ አባላት ተከባብረውና ተቻችለው ይኖሩ ዘንድ ችግሩ ትኩረት ተሰጥቶት ዘላቂ መፍትሄ ይበጅለት ዘንድ ኢሰመጉ በድጋሚ ይጠይቃል፡፡

ለሰብአዊ መብቶች መከበርና ለሕግ ልዕልና የቆማችሁ ዜጎች፣ ብሔራዊና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች፣ የመንግሥታትና የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ተወካዮች ዜጎች በህግ የተረጋገጡላቸው መብቶች እንዲከበሩላቸውና የኢትዮጵያ መንግስት በአገሪቱ ህገመንግስት የተረጋገጡትን መብቶች ለሁሉም ዜጎች በእኩልነት እንዲያስከብር የበኩላችሁን ግፊት ታደርጉ ዘንድ ኢሰመጉ ይጠይቃል፡፡

**ግልባጭ**

- **ክቡር አምባሳደር ተሾመ ቶጋ**
  *የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት አፈጉባኤ*
  *ፖ.ሣ.ቁጥር 80001፣ ፋክስ (251-11) 155 0900*
  *ስልክ (251-1) 1241013*
  *አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ*

- **ክቡር አቶ ደግፌ ቡላ**
  *የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፌዴሬሽን ም/ቤት አፈ ጉባኤ*
  *ፖ.ሣ.ቁጥር 80001፣ ፋክስ (251-11) 155 0722*
  *ስልክ (251-11) 124 2301*
  *አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ*

- **ክቡር አቶ ግርማ ወ/ጊዮርጊስ**
  *የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፕሬዚዳንት*
  *ፖ.ሣ.ቁጥር 1031፣ ፋክስ (251-11) 155 2020*
  *ስልክ (251-11) 551 8850*
  *አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ*

- **ክቡር አቶ መለስ ዜናዊ**
  *የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር*
  *ፖ.ሣ.ቁጥር 1031፣ ፋክስ (251-11) 155 2020*
  *ስልክ (251-11) 122 6767*
  *አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ*

- **ክቡር አቶ ሲራጅ ፈርጌሣ**
  *የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስትር*
  *ፖ.ሣ.ቁጥር 1370፣ ፋክስ (251-11) 552 0000*
  *ስልክ (251-11) 552 0000*
  *አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ*

- **ክቡር አቶ አሰፋ ከሲቶ**
  *የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፍትሕ ሚኒስትር*
  *ፖ.ሣ.ቁጥር 1370፣ ፋክስ (251-11) 552 0874*
  *ስልክ (251-1) 551 5099*
  *አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ*

- **ክቡር አቶ ፍቅሩ ኛካል**
  *የደቡብ ብሔር፣ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ*
  *ፖ.ሣ.ቁጥር 18፣ ፋክስ (251-46) 220 1950*
  *አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ*

- **ክቡር አምባሳደር ካሣ ገ/ሕይወት**
  *የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር*
  *ፖ.ሣ.ቁጥር 1165፣ ፋክስ (251-11) 645 9290*
  *ስልክ (251-1) 645 9228*
  *አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ*

- **ክቡር አቶ አባይ ተክሌ**
  *የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ዋና እምባ ጠባቂ*
  *ፖ.ሣ.ቁጥር 2459፣ ፋክስ (251-11) 645 9229*
  *ስልክ (251-11) 663 5090፣ 663 5363*
  *አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ*